# የዘር መከፋፈል ግድግዳ የፈረሰ ይሁን!

ግርማ ካሳ
muziky68@yaho.com

11 መጋቢት 2001

በግምት ከአሥራ አራት አመታት በፊት ይሆናል ቀኑ። በኢትዮጵያ እርቅና ሰላም እንዲኖር ብዙ ጊዜ የሚደክሙና የሚጸልዩ፣ ቄስ ቶሎሳ ጉዲና የሚባሉ አንድ መንፈሳዊ አባት፣ ምእመናንን ሲያስተምሩ የተናገሩት፣ ሁልጊዜ የማስታወሰዉና የማልረሳዉ አባባል ነበር።

«አዲስ አበባ አንድ ወዳጄ አርፎ ለቀብር ሄድኩኝ። የወዳጄ የቀብር ሥነ-ስርዓቱ ካለቀ በኋላ ሌሎች ወደ ቤታቸዉ ሲመለሱ እኔ በዚያዉ ቆየሁ። በመቃብሩ ቦታ ያሉትን ኃዉልቶች እያየሁ በድንጋዮቹ ላይ የተጻፉትን የሚችቹን ስምና መንፈሳዊ ጥቅሶች ማንበብ ጀመርኩኝ። ዘር ስል አንዱ መቃብር ላይ የትግሬ ስም አየሁ። ሄድ ብዬ ደግሞ እንደኔዉ በ "ሳ" የሚያልቅ የኦሮሞ ስም ያለበት ኃዉልት አጋጠመኝ። የአማራም የሚመስልም አለ። እንግዲህ አስቡት ... ትግሬዉም አማራዉን ኦሮሞዉም ... ሁሉም በሰላም ተኝተዋል» ሲሉ እኚህ መንፈሳዊ አባት የታዘቡትን ተረኩ። ምን ለማለት ፈልገዉ እንደሆነ መጀመሪያ ላይ አልገባኝም ነበር።

አይኖቻቸዉን ወደ ምእመኑ አድርገዉ «ሙታን አርፈዉ በሰላም ጸጥ ብለዉ ተኝተዋል። እኔ ትግሬ ነኝ፣ አንተ አማራ ነህ፣ ደግሞ ጉራጌ ሆነህ እኔ ጋር ምን ታደርጋለህ ? እያሉ አይገፋፍሙም። በሰላም ጸጥ ብለዉ ነዉ ጎን ለጎን የተኙት» ሲሉ ትምህርታቸዉን ቀጠሉ።

ምእመናን በተመስጦ ያዳምጡ ነበር ። እኚህ አባት ለትንሽ ጊዜ ዝም አሉና ከኪሳቸዉ ዉስጥ ማህረባቸዉን አወጡ። በአይናቸዉ ላይ የነበረዉን እንባ ጠረጉ። ትልቅ ትንፋሽ ተንፍሰዉ «ታዲያ ... እኛ በሕይወት ያለን ሕያዋን፣ በእግዚአብሄር እንድንዋደድና እንድንፋቀር፣ አንዱ ለሌላዉ እያዘነና እየተከባበርን እንድንኖር በመልኩና በአምሳሉ ፈጥሮን፣ ሁላችንም የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን፣ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ሆነን፣ እንዴት አብረን ተፋቅረን በሰላም መኖር ያቅተናል ? ስለምን ሰዉን በስብዕናዉና በኢትዮጵያዊነቱ ከማክበርና ከመቀበል ይልቅ በዘር እየተከፋፈልን እንደጠላት እንተያያለን ? » በማለት ለምእመናኑ ጥያቄዎች አቀረቡ።

«ይኼ መርገም ነዉ። ይኼ በሽታ ነዉ። ይኼ ከሙታን የባሰን እንደሆንን የሚያሳይ ነዉ። እግዚአብሄር ከዚህ እርግማን ያዉጣን ! እግዚአብሄር አገራችን ኢትዮጵያንም መልካም ጣቶቹን ዘርግቶ ይፈወሳት ? » ሲሉ፣ ምእመናን ከተቀመጡበት ብድግ ብለዉ «አሜን» አሉ።

ከአሥራ ስድስት አመታት በፊት ደግሞ ሌላ የሰማሁት አንድ ታሪክ ነበር። ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ከዘር ጋር በተገናኘ መዘዝ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን ማለቃቸዉ መቼም የሚረሳ አይደለም። (አሁንም ያ አይነት ችግር በአገራችን አለ)

ያኔ በበደኖ፣ በአርባጉጉ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች ኢትዮጵያዉያን፣ ከኛ ዘር አይደላችሁም ተብለዉ፣ በጭካኔ ከመቶ ሜትር በላይ በሚሆን ገደል ዉስጥ አይናቸዉ በጨርቅ ተሸፍኖ፣ ነፍሰ ጡር የሆኑ ሴቶች ሁሉ ሳይቀር ተወርዉረዋል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቤታቸዉ ዉስጥ እያሉ እንዲቃጠሉ ተደርጓል። በጣም የሚያሳዝንና የማይረሳ ግፍ በኢትዮጵያዎኖች እጅ ኢትዮጵያዉያኖች ላይ ተፈጽሟል።

የቂም በቀልና የዘረኝነት ደመና አገሪቷን በሸፈነበት በዚያን ወቅት፣ በኢሊባቡር ክፍለ ሃገርም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈጠር በዘራቸዉ ምክንያት ዜጎች ይጠቁ ዘንድ የሚገፋፋ ርካሽ ቅስቀሳ ማድረግ ተጀመረ። ("አማራ" የሚባለዉ ከ"ኦሮሞዉ" ጋር እንዲገዳደል)

የሚያስደንቀዉ ነገር ግን በዚያ የሚኖሩ አበዉና ሽማግሌዎች፣ ወጣቶችን ሰብስበዉ **«ለዘማናት አብረን ኖረናል። ተዋልደናል። ተጋብተናል። የነርሱ ልጆች የኛ ልጆች ናቸዉ። እነርሱን ማጥፋት እኛን ማጥፋት ነዉ»** ብለዉ ፍቅርንና አንድነትን አስተማሩ። ለዚህ ይመስለኛል በአርባ ጉጉና በበደኖ የታየዉ አይነት እልቂት በኢሊባቡር ተፈጸመ ሲባል ያልተሰማዉ።

ከሁለት ሺህ አመታት በፊት ወደ ሆነ ሌላ አንድ አስደናቂ ታሪክ ልዉሰዳቹህ። አገሩ በመካከለኛዉ ምስራቅ ነበር። ሁለት ህዝቦች ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ አይሁዳዉያን ይባላሉ። ሁለተኞቹ ደግሞ ሳምራዉያን ይባላሉ። አይሁዳዉያንና ሳምራዉያን አይስማሙም ነበር። ፊት ለፊት ተያይተዉ እንኳን ሊነጋገሩ፣ አንዳቸዉ ወደ አንዳቸዉ ምድር አይደርሱም ነበር። በተለይም

አይሁዶች ሳምራዉያንን እንደሐጢያተኛ ይቆጥሯቸዉ ስለነበር ፣ ከነርሱ ጋር ከተገናኙ እንደሚረክሱ አድርገዉ ነበር የሚያስቡት።

እዚህ ላይ፣ በዚያን ወቅት የነበረዉ ባህልና ልማድ፣ የጥላቻ፣ የመናናቅና የዘረኝነት እንደነበረ እናያለን። በሰዎችና በሰዎች መካከል የሚለያይና የሚከፋፈል ሰዉ ሰራሽ ትልቅ ግንብ እንደነበረ እናያለን።

በዚህ ወቅት ነዉ እንግዲህ አንድ ሰዉ፣ የነበረዉንና የጊዜዉን ሁኔታ ወደ ጎን በማድረግ፣ አይሁዳዊ ሆኖ ሳለ ሳምራዉያን ወደ ሚኖሩበት ሰማሪያ ክፍለ ሃገር ያመራዉ። በዚያም አንዲት ሳምራዊት ሴትን፣ ሲካር በምትባል በሰማሪያ ባለች ከተማ በሚገኝ በዉሃ ጉዳጋድ አጠገብ አገኛትና አናገራት። ዉሃ ቀድታ እንድትሰጠዉ ጠየቃት።

ሳምራዊቷ ሴትም፣ ይህ አይሁዳዊ ሰዉ፣ እረከሳለሁ ብሎ ሳያስብ፣ ሳይፈራ፣ ከተለመደዉ ጎጂ ባህል ዉጭ በመሆን እርሷን ማናገሩ በጣም አስገርሟት «አንተ አይሁዳዊ ሆነህ ሳለህ እኔ ሳምራዊቷን እንዴት ዉሃ አጠጪኝ  ትለኛለህ ? » ስትል ጠየቀቻዉ።

ይህ ሰው እስላም ወንድሞቻችን ኢሳ የሚሉት፣ ክርስቲያኖች የሆንን ደግሞ አንዳንዴ መድሃኔዓለም አንዳንዴ አማኑኤል ብለን የምንጠራዉና የምናመልከዉ፣ ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ።

**«ሳምራዊ» ወይም «አይሁዳዊ» እያሉ በዘር መከፋፈል ሐጢያት እንደሆነና እግዚአብሄር እንደማይወደዉ ነዉ እዚህ ላይ የምናየዉ። በዚያን ወቅት የነበረዉን ጎጂ የዘረኝነት ግድግዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያፈርሰዉ ነዉ የምናየዉ። ሰዉ ከሰዉ ጋር በዘሩ ምክንያት መራራቅና መከፋፈል እንደሌለበት ነዉ የምንማረዉ። ሁሉም ሰዉ የእግዚብሄር ልጆች እንደመሆናቸዉ ወንድማማቾችና እህትማማቾች እንደሆኑ ነዉ የምናየዉ።**

በቅርቡ በባህር ዳር ከተማ በሚገኝ ዩኒቨርስቲ ከዘር ጋር በተገናኘ በተማሪዎች መካከል ችግር መፈጠሩ በሰፊዉ ተዘግቧል። እንዲህ አይነቱ ችግር በአገራችን ባሉ ከፍተኛ ተቋሞች ሲታይ የመጀመሪያዉ አይደለም። ዮኒቨርሲቲዎች፣ ዜጎች በእዉቀትና በትምህርት እንዲያድጉ የሚረዱ ተቋማት ናቸዉ።

የአለም ህብረተሰብ ከዘረኝነት አልፎ በጋራ መሥራት በጀመረበት ወቅት፣ በአገራችን ባሉ ዮኒቨርሲቲዎች ይህ አይነት ከዘር ጋር የተገናኙ ችግሮች መፈጠራቸዉ እጅግ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነዉ። የተማርን እንደመሆናችን የበለጠ መብሰልና ማገናዘብ ሲገባን፣  በሰይጣን መንፈስ የሚንቀሳቀሱ ጥቂት ግለሰቦች ለግል ጥቅማቸዉ የሚያናፍሱትንና የሚቆሰቁሱትን የጥላቻና የዘረኝነት ፖለቲካን በማስተናገድ፣ ለጥቂቶች መጠቀሚያ እስከንሆን ድርስ ማስተዋል ማጣታችን ያሳዝናል። ምኑ ላይ ነዉ ታዲያ መማራችን?

የተለያዩ ቀለማት ባላቸዉ ክሮች የተሰራ ሹራብ ያምራል። ብርድና ንፋስ በመጣ ጊዜ ሲለበስ ይሞቃል። ነገር እያንዳንዳችን አንድ ቀለም ለይተን ክሮችን መምዘዙንና መተርተሩን ከቀጠልንበት ክሮቹ ተመዘዉ፣ ተመዘዉ እርስ በርስ ተወሳሰበዉ ጥቅም የለሽ ይሆናሉ። ብርድ በመጣ ጊዜ ለብሰን የምንሞቅበት ሹራብ አይኖረንም። **እጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ ካላደግን ሁላችንም አብረን እንጠፋለን።**

አላስተዋልንም እንጂ በአሁኑ ወቅት በራሳችን እጅ እየጠፋን ነዉ ያለነዉ። የኛን አገርን ጨምሮ አንዳንድ የአፊሪካ መሪዎች ጂ-ሃያ ለተበለዉ ስብሰባ ትልቅ ዝግጅት እያደረጉ ናቸዉ። ዝግጅቱ ለምን እንደሆነ የማናወቅ ያለን አይመስለኝም። ለመለመን ነዉ !

እንግዲህ ከዚህ የበለጠ መሞት አለን ? ከዚህ የበለጠ ዉርደት አለን ? አባይ፣ ሸበሌ፣ ተከዜ፣ አሞ፣ አዋሽ የመሳሰሉ ታላላቅ ወንዞች እያሉን፣ በየጊዜዉ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝባችን ለረሃብና ለችጋር ሲጋለጥ ማየቱና የምንበላዉን ዳቦ የምንጋግርበት ዱቄት ለዝንተ ዓለም ከፈረንጆች መለመን መሞት አይደለምን ? መንግስት ያልነበራት ሶማሊያ እንኳን እንደኛ በረሃብ አልተጠቃችም። የትላንትናዎቹ እንደ ጋና፣ ሴኔጋል ያሉ የአፍሪካ አገራትማ የትናየት ጥለዉን ሄድዋል ።

ወገኖቼ ፣

ፍቅርና ሰላም ቢኖር ፣ አሁን በስልጣን ላይ ያሉ ባለሥልጣናት በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ላይ የሚያራምዱትን የእልህና የግፍ ፖለቲካ ቢያስወግዱ፣ ወደ መሐል  መጥተዉ ከተቀረዉ ኢትዮጵያዊ ጋር በትህትና የአገራችንን ችግር ለመፍታት ቢነጋገሩ ፣ ዳያስፖራዉን እንደ “ሰይጣን” ከማየትና ከማጥላላት ከዳያስፖራዉ ጋር ቅንነት ያለበት ንግግር ቢጀመሩ እኮ  የነ ጎርደን ብራዉንን ጫማ ልሶ ፍርፋሪ ዶላር ከማግኘት፣ ዉጭ አገር ከሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር የዉጭ ምንዛሪ መሰብሰብ ይቻል ነበር። ብዙ ብዙ ብዙ ነገራት በጋራና በአንድነት ማከናወን ይቻል ነበር።

እንግዲህ የዘር ፖለቲካ ይቁም ! የሰብአዊ መብት ረገጣ ይቁም ! ሕገ የበላይ ይሁን ! ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች በግፍ የታሰሩ ሰላማዊ ዜጎች በአስቸኳይ ይፈቱ ! ሁላችንም ወደ እርቅ እንምጣ ! ሁላችንም በዘር ሳንከፋፈል በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር እንሰባሰብ ! እግዚአብሄር የሰጠንን አንዲት ኢትዮጵያ ከዉርደትና ከማቅ ነጻ እናውጣት !

ለአንዳንዶቻችን ይህ ቅዠትና ሕልም ሊመስለን፣ በሽንፈትና በአይቻልም መንፈስ በመያዛችን በዉስጣችን ጨለምተኝነት ሊኖር ይቻላል። አንዳንዶቻችን ደግሞ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ሙሉ ለሙሉ ተስፋ የቆረጥን እንኖራለን። ነገር ግን ሁላችንም ልናያት የምንፈልገዉን አዲሲቷን ኢትዮጵያ ማየት እንችላለን። አገራችንን አሁን ካለችበት የሃያ አንደኛዉ ክፍለ ዘመን ቅኝ ግዛት (High Tech colonization ) ነጻ ማወጣት እንችላለን። እራሳችን በራሳችን መመገብ እንችላለን።

የሚያስፈልገዉ የልብና የአይምሮ ለዉጥ ፣ መንፈሳዊ ፈዉስና በአፍ ብቻ ሳይሆን በእዉነትና በመንፈስ እጆቻችን ወደ እግዚአብሄር መዘርጋት ነው ! «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች» የተባለዉ የተስፋ ቃል ይፈጸም ዘንድ እኛ ኢትዮጵያዉያን እጆቻችንን ከልባችን ጋር ወደ እግዚአብሄር እንዘርጋ !

በሳምራዉያንና በአይሁዳዊያን መካከል የነበረዉን ግድግዳ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳፈረሰዉ አሁንም በኢትዮጵያውያን መካከል ያለዉን የዘረኝነትና የመከፋፈል ግድግዳ ያፈራርስልን ! የይቅርታንና የመቀራረብን መንፈስ ያወርድልን ! እግዚአብሄር ሁላችንንም ይርዳን !